## የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 5 /2014

## በሃገር ህልውና እና ሉዐላዊነት ላይ የተደቀነን አደጋ ለመከላከል የወጣ

## የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ

መንግሥት የሃገርን ህልውና፣ ሉዐላዊነት እና የግዛት አንድነት ከውስጥም ሆነ ከውጭ ጠላቶች የመጠበቅ የሕግም ሆነ የሞራል ኃላፊነት እና ግዴታ  ያለበት መሆኑን በመገንዘብ፣

የሽብርተኛው ሕውሃት እና የሽብር ግብረአበሮቹ እንቅስቃሴ በሃገር ህልውና እና ሉዐላዊነት ላይ ጉልህ እና ድርስ አደጋ የደቀነ በመሆኑ፣

ሽብርተኛው ሕውሃት እና የሽብር ግብረአበሮቹ ለዕኩይ አላማቸው መሳካት በተለያዩ የሃገራችን አካባቢዎች በንፁሃን ዜጎች ላይ እየፈፀሙ ያሉት  ግድያ፣ ዝርፍያ  እና ሌሎችም ከፍተኛ ጭካኔ የተሞላባቸው ኢሰብዐዊ ጥቃቶች እጅግ አደገኛ ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ከግምት በማስገባት፣

ከቀጥተኛ እና መደበኛ የውጊያ አውድ በተጨማሪም የሽብርተኛው ሕውሃት እና የሽብር ግብረአበሮቹን ተልዕኮ ያነገቡ ግለሰቦች ከሰላማዊ ዜጎች ጋር በመመሳሰል በህዝብ እና በሃገር ላይ የደቀኑትን  ከፍተኛ እና ተጨባጭ የደህንነት ስጋት በመረዳት፣

ሽብርተኛው ሕውሃት  ኢትዮጵያን የማዳከም እና ብሎም የማፍረስ ምኞት ካላቸው የውጭ ሃይሎች ጋር በከፍተኛ ቅንጅት እየሰራ እንደሆ በመገንዘብ ፣

ከላይ የተገለፁት የሃገር ህልውና ላይ የተደቀኑ አደጋዎችን በመደበኛው የሕግ ማስከበር ሥርዓት ለመቋቋም አዳጋች በመሆኑ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መደንገግ እና ተግባራዊ ማድረግ  አደጋውን ለመቀልበስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 93/1/ሀ መሰረት የሚከተለው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታውጇል::

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

### 1. አጭር ርእስ

ይህ አዋጅ ***"የሃገርን ሀልውና እና ሉዐላዊነት ላይ የተደቀነን አደጋ ለመከላከል የወጣ አዋጅ ቁጥር 5/2014"*** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. ትርጓሜ

ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል፤

1. **"የሕግ አስከባሪ አካል"** ማለት የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የክልል ፖሊስ እና ሌሎች የፀጥታ አካላት ማለት ነው።
2. **"የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ"** ማለት የዚህን አዋጅ አፈጻጸም ለመከታተል እና በበላይነት ለመመራት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 መሠረት የተቋቋመ የአስቸኳይ ጊዜ መምሪያ ዕዝ ነው።
3. **"የጦር መሳሪያ"** ማለት በጦር መሳሪያ አስተዳደር ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 ትርጉም የተሰጣቸውን አነስተኛ፣ ቀላል እና ሌሎችንም የጦር መሳሪያ አይነቶች እና ጉዳት አድራሽ ዕቃዎች ያጠቃልላል።
4. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው።
5. በዚህ አዋጅ በወንድ አነጋገር የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል።

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ አዋጅ በመላው ኢትዮጵያ ተፈፃሚ ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአደጋው መጠን እና አካባቢያዊ አድማስ እየቀነሰ በሄደ ጊዜ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የተፈፃሚነት ወሰን በዚያው ልክ እየጠበበ ሊሄድ የሚችል ሲሆን፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ አዋጁ ተፈፃሚነት በከፊልም ሆነ በሙሉ ቀሪ የሚሆንባቸውን አካባቢዎች በመመሪያ ይወስናል፤ ይህንን ለሕዝብ ያሳውቃል።

## ክፍል ሁለት

## በአስቸኳይ ጊዜ የሚወሰዱ እርምጃዎችና የማይፈቀዱ ተግባራት

### 4. በአስቸኳይ ጊዜ የሚወሰዱ እርምጃዎች

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ የሃገርን ህልውና እና ሉዐላዊነት፣ እንዲሁም የሰላማዊ ዜጎችን ደህንነት ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን፡-

1. በየትኛውም የሃገሪቱ ክፍል መከላከያ ኃይልን ወይም የትኛውንም ሌላ የጸጥታ አካል በማሰማራት ሰላምና ፀጥታ እንዲያስከብሩ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤
2. እድሜያቸው ለወታደራዊ አገልግሎት የደረሱ እና የጦር መሳርያ የታጠቁ ዜጎች ወታደራዊ ስልጠና እንዲወስዱ፣ ወታደራዊ ግዳጅ እንዲቀበሉ፣ ወይም ይህን ማድረግ የማይችሉ ሲሆን በእማራጭ ትጥቃቸውን ለመንግስት እንዲያስረክቡ ሊያዝ ይችላል፤
3. የሰዓት ዕላፊ ገደብ ሊወሰን ይችላል፤
4. ማናቸውም የህዝብ የመገናኛ እና የህዝብ መጓጓዥ ዘዴ እንዲዘጋ ወይም እንዲቋረጥ ሊያዝ ይችላል፤
5. ከሽብር ቡድኖች ጋር ይተባበራል ብሎ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የተጠረጠረ ማንኛውንም ሰው ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በቁጥጥር ሥር ለማድረግ፣ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ ሆኖ ባለበት ጊዜ ድረስ ይዞ ለማቆየት ወይም በመደበኛ ሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ለማድረግ ይችላል፤
6. ከሽብር ቡድኖች ጋር ይተባበራል ብሎ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የተጠረጠረ ማንኛውንም ሰው ወይም ድርጅት ንብረት የሆነን ማናውንም ቤት፣ ህንፃ፣ ቦታ፣ መጓጓዣ ለመበርበርና እንዲሁም ማንኛውንም ሰው ለማስቆም፣ ማንነቱን ለመጠየቅ፣ ለመፈተሽ ይችላል፤ በብርበራ ወይም በፍተሻ የተያዙ የጦር መሳሪያዎችን መውረስ ይችላል ፤
7. ለተወሰነ ጊዜ መንገዶችን፣ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ለመዝጋት እንዲሁም ሰዎች ለጊዜው በተወሰነ ቦታ እንዲቆዩ፣ ወደ ተወሰነ አካባቢ እንዳይገቡ ወይም ከተወሰነ ቦታ እንዲለቀቁ ለማዘዝ ይችላል፣
8. ከፍተኛ የፀጥት ችግር እና ስጋት በተፈጠረባቸው የሃገሪቱ ክፍሎች የአካባቢ አመራር መዋቅርን በከፊልም ሆነ በሙሉ፣ ማገድ፣ መለወጥ እና በሲቪልም ሆነ በወታደራዊ አመራር መተካት ይችላል፤

9. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሽብር ቡድኖች የሞራልም ሆነ የቁስ ድጋፍ ያደርጋል ብሎ የሚጠረጥረውን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት እንቅስቃሴ በሚመለከተው ባለስልጣን በኩል እንዲታገድ ወይም ፍቃዱ እንዲሰረዝ ሊያዝ ይችላል፤

10. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሽብር ቡድኖች የሞራል ድጋፍ ያደርጋል ብሎ የሚያምነውን የመገናኛ ብዙሃንን ወይም ጋዜጠኛ በሚመለከተው ባለስልጣን በኩል እንዲታገድ ወይም ፍቃዱ እንዲሰረዝ ሊያዝ ይችላል፤

## 5. ተመጣጣኝ ሀይል ስለመጠቀም እና የማይታገዱ መብቶች

1. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎችን ለማስፈጸም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሕግ አስከባሪ አካላት ተመጣጣኝ ኃይል እንዲጠቀሙ መመሪያ ለመስጠት ይችላል።

2. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ በሚያወጣቸው መመሪያዎችም፣ በሚወስናቸው ውሳኔዎች እና በሚወስዳቸው እርምጃዎች በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 93(4)(ሐ) መሰረት ሊታገዱ የማያችሉ የሕገ መንግስት ድንጋጌዎችን እና መብቶችን ማክበር ይኖርበታል።

## 6. የተከለከሉ ተግባራት እና ግዴታዎች

1. ሁሉም ሰው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ በአዋጁ መሰረት የሚያወጣቸውን መመሪያዎች እና የሚሰጣቸውን ትዕዛዞች የመቀበል ግዴታ አለበት።

2. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙን እንቅስቃሴ እና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን አላማ የሚቃረን፣ የሚቃወም እና ለሽብር ቡድኖች አላማ መሳካት አስተዋፅዖ የሚያደርግ፣ የሽብር ቡድኖችን የሚያበረታታ፣ ሰላማዊ ዜጎችን የሚያሸብር ንግግር በማንኛውም መንገድ ማድረግ ወይም ማሰራጭት የተከለከለ ነው።

3. በየትኛውም መንገድ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሽብር ቡድኖች የገንዘብ፣ የመረጃ፣ የቁስም ሆነ የሞራል ድጋፍ ማድረግ የተከለከለ ነው።

4. አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ በተዋረድ ውክልና ከሰጣቸው አካላት ፈቃድ ውጪ ማንኛውንም የአደባባይ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ የተከለከለ ነው።

5. ከመከላከያ፣ ከፌዴራል ፖሊስ ወይም ሌሎች ፈቃድ ከሚሰጣቸው የፀጥታ አካላት ወይም ከነዚህ አካላት እውቅና እና ፈቃድ ውጭ ማናቸውንም የጦር መሳርያ ይዞ መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው።

6. በከተሞች አካባቢ የነዋሪ መታወቂያ ፣ የመንጃ ፈቃድ፣ የሰራተኛ መታወቂያ፣ ፓስፖርት ወይም ከነዚህ ተመጣጣኝ የሆነ መታወቂያ ሳይዙ መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው። ከነዚህ የመታወቂያ ሰነዶች መካከል የትኛውም የሌለው ሰው ይህን ጉዳይ በተመለከተ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ ዝርዝር የአፈፃጸም መመሪያ ባወጣ በሁለት ሳምንት ውስጥ በአቅራቢያው በሚገኝ የቀበሌ፣ የወረዳ የፀጥታ እና አስተዳደር ፅህፈት ቤት ወይም ፖሊስ ጣቢያ በመመዝገብ ጊዜያዊ የመታወቂያ ወረቀት የመያዝ ግዴታ አለበት።

7. ማንኛውንም ወሳኝ በሆነ የአገልግሎት ዘርፍም ሆነ በምርት ሂደት ላይ የስራ ማስተጓጎል ወይም የኢኮኖሚ አሻጥር መፈፀም የተከለከለ ነው።

8. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን አፈፃፀም ሰበብ በማድረግ የግል ጥቅም ለማግኘት ስልጣንን አላግባብ መጠቀም፣ ምክንያታዊ የሆነ ጥርጣሬ ሳይኖር ሆን ብሎ ዜጎችን ማሰር ወይም መሰል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው።

## ክፍል ሶስት

## ስለ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ

### 7. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ መቋቋምና ኃላፊነት

1. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን የሚያስፈፅም በኢፌድሪ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም የሚመራ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ ተቋቁሟል።
2. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መመርያ ዕዙ መዋቅር እና አደረጃጀት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚወሰን ይሆናል።
3. አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ አግባብነት ካላቸው አካላት የተወጣጡ እና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ሃላፊነት ወስደው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ተፈፃሚ የሚያደርጉ ግብረሃይሎችን ወይም ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል።

4. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ ተጠሪነት ለ ኢ.ፌ.ድ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናል።
5. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 የተመለከቱ እርምጃዎችን ተፈጻሚነት ይመራል፣ ይከታተላል።
6. አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ በሃገሪቱ የሚገኙ የሕግ አስከባሪ አካላትን በአንድ ዕዝ ሥር እድርጎ በላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ያዛል።
7. ኃላፊነቱን ለመወጣት ሌሎች አስፈላጊ እና አግባብ የሆኑ ስልጣኖች ይኖሩታል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### 8. ተፈፃሚነታቸው የታገዱ ሕጎች

1. በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እሲኪጠናቀቅ ድረስ የትኛውም የዳኝነት አካል ስልጣን አይኖረውም።

2. በቪዬና ኮንቬንሽን የተመለከተው የዲፕሎማቲክ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ የፍሬ ነገርና የሥነ ሥርዓት ሕጎች ይህ አዋጅ በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ተፈፃሚነታቸው ታግዶ ይቆያል::

### 9. የወንጀል ተጠያቂነት

1. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በአዋጁ መሰረት የወጡ መመሪያዎችን ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው እስከ ሶስት አመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም እንደጥፋቱ ክብደት እስከ አስር አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

2. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በአዋጁ መሰረት የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ የተፈፀመው ወንጀል በሌሎች ሕጎች ከዚህ ከፍ ያለ ቅጣት የሚያስከትል ከሆነ የከበደው ቅጣት ተፈጻሚ ይሆናል።

3. በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ወቅት የተፈፀሙ የአዋጁ እና በአውጁ ማዕቀፍ የወጡ መመሪያዎች ጥሰቶች የአዋጁ ተፈጻሚነት ጊዜ ቢያበቃም፣

የሚያስከትሉት የወንጀል ተጠያቂነት በመደበኛው የወንጀል ሥነ ስርዐት ሕግ መሰረት ይቀጥላል።

## 10. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ በአዋጁ የተሰጠውን ስልጣን ተግባራዊ ለማድረግ እና ሃላፊነቱን ለመወጣት አስፈላጊ መመሪያዎችን ያወጣል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የሚወጡ መመሪያዎች ተፈፃሚ ከመደረጋቸው በፊት ለህዝብ በስፋት ተደራሽ በሆኑ የመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ እንዲተዋወቁ መደረግ ይኖርበታል።

## 11. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

1. ይህ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከታወጀበት ጊዜ ጀምሮ ለስድስት ወራት የፀና ይሆናል።

2. የስድስት ወር ጊዜ ገደቡ ከመጠናቀቁ በፊት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአዋጁ ተፈፃሚነት ቀሪ የሚሆንበትን ጊዜ ሊወስን ይችላል።

**አዲስ አበባ ጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ/ም**

**ዐብይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበለትን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መርምሮ ማጽደቁን ተከትሎ፤ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ መዋቅር እና አደረጃጀት መመሪያ ይፋ ሆኗል።

በዚሁ መሠረት “የሃገርን ህልውና እና ሉዐላዊነት ላይ የተደቀነን አደጋ ለመከላከል የወጣ አዋጅ ቁጥር 5/2014” ተብሎ ነው ይፋ የሆነው።

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ መዋቅር እና አደረጃጀት መመሪያውም እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ መዋቅር እና አደረጃጀት መመሪያ

የአስቸኳይ ጊዜ 5 /2014 መመሪያ ቁጥር 1/2014

“የሃገርን ህልውና እና ሉዐላዊነት ላይ የተደቀነን አደጋ ለመከላከል የወጣ አዋጅ ቁጥር 5/2014”፣ አንቀጽ 7 (1) የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን የሚያስፈፅም፣ ለኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር እና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ተጠሪ የሆነ በኢፌዴሪ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም የሚመራ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ ያቋቋመ ሲሆን ÷ በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ(2) አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምርያ ዕዙ መዋቅር እና አደረጃጀት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚወሰን እንደሆነ ተመላክቷል።

በዚሁ መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ መዋቅር እና አደረጃጀት እንደሚከተለው እንዲሆን ተወስኖ ይህ መመሪያ ወጥቶዋል።

1. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ መዋቅር እና አደረጃጀት እነዚህ መሰረት በፌደራል እና በክልል ደረጃ የአዋጁን አፈፃፀም እንዲከታተሉ ከዚህ በታች የተመላከቱት ኮሚቴዎች ተቋቁመዋል፤

1) የፌዴራል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የክትትል ኮሚቴ፤

2) የፌዴራል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ የፀጥታ ኮሚቴ፤

3) የክልል’ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ ኮሚቴ፤

2) ተጠሪነት

ከዚህ በላይ የተመለከቱት ኮሚቴዎች ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው። ኮሚቴዎቹ የስራ አፈፃጸማቸውን አስመልክቶ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባሉ።

3. የኮሜቴዎቹ ሃላፊነት

4. በፌዴራል እና በክልል ደረጃ የአዋጁን አፈፃፀም እንዲከታተሉ የተቋቋሙት ኮሜቴዎች ሃላፊነት እንደሚከተለው ይሆናል፤

ሀ) የፌዴራል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የክትትል ኮሚቴ ሃላፊነት፤

1.የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን አፈፃፀም ጋር በተገናኘ ያሉ የፖለቲካ፣ የዲፕሎማሲ እና የህዝብ ግንኙነት ስራዎችን ማስተባበር እና መከታተል፤

2. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን አላማ ለማሳካት የሚሰሩ የህዝብ አደረጃጀት እና እንቅስቃሴ ስራዎችን ማስተባበር እና መከታተል፤

3. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን አፈፃፀም ጋር በተገናኘ የሚኖሩ የህዝብ ቅሬታዎች ምላሽ እንዲያገኙ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፤

4. በሽብርተኛው ቡድን የተፈናቀሉ እና ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ማሳለጥ፤

ለ) የፌዴራል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ የፀጥታ ኮሚቴ ሃላፊነት፤

1. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን የቀን ተቀን አፈፃፀም በፌዴራል ደረጃ መምራት፣ ማስተባበር እና መከታተል፤

2. በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የተደነገጉ ክልከላዎች እና ግዴታዎችን ተፈጻሚነት ማረጋገጥ፤

3. ሁሉንም ፀጥታ፣ የደህንነት እና የህግ አስከባሪ አካላት በተቀናጀ ሁኔታ እንዲንቀሳቀሱ ማስቻል፤

4. ለአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መሳካት አስፈላጊ የሆኑ ኦፕሬሽኖችን በቅንጅት ማቀድ እና ተግባራዊ ማድረግ፤

ሐ) የክልል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ ኮሚቴ ሃላፊነት

1. በዞን፣ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን የሚያስፈፅሙ ግብረ-ሃይሎችን ማቋቋም፤

2. በክልል ደረጃ ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን አፈፃፀም ጋር በተገናኘ ያሉ የፖለቲካ እና የህዝብ ግንኙነነት ስራዎችን ማስተባበር እና መከታተል፤

3. በክልል ደረጃ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን አላማ ለማሳካት የሚሰሩ የህዝብ አደረጃጀት እና እንቅስቃሴ ስራዎችን ማስተባበር እና መከታተል፤

4. በክልል ደረጃ ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አፈፃፀም ጋር በተገናኘ የሚኖሩ የህዝብ ቅሬታዎች ምላሽ እንዲያገኙ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፤

5. በክልል ደረጃ በሽብርተኛው ቡድን የተፈናቀሉ እና ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ማሳለጥ፤

6. ከፌዴራል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ የፀጥታ ኮሚቴ ጋር በተናበበብ መንገድ በክልሉ የፀጥታ ማስከበር ስራዎችን መምራት፣ ማስተባበር እና መከታተል፤

4) የኮሜቴዎች ስብጥር

በፌዴራል እና በክልል ደረጃ የአዋጁን አፈፃፀም እንዲከታተሉ የተቋቋሙት ኮሜቴዎች ስብጥር እንደሚከተለው ይሆናል፤

ሀ) የፌዴራል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የክትትል ኮሚቴ

1. አቶ ደመቀ መኮንን (ም/ጠ/ ሚኒስትር እና የው/ጉ/ሚኒስትር) – ሰብሳቢ
2. ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ – አባል
3. አቶ በለጠ ሞላ – አባል
4. አቶ አቶ ቀጀላ መርዳሳ – አባል
5. ኢንጂነር አይሻ መሐመድ – አባል
6. ዶ/ር ኤርጎጌ ተስፋዬ – አባል
7. ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ – አባል
8. አቶ ሬድዋን ሁሴን – አባል
9. አቶ ምትኩ ካሳ – አባል

ለ) የፌደራል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ የፀጥታ ኮሚቴ

1. ጄ/ል ብርሃኑ ጁላ( የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም) – ሰብሳቢ
2. የብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጄነራል – አባል
3. የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽነር – አባል
4. የፍትህ ሚኒስትር – አባል
5. የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት – አባል

ሐ) የክልል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ ኮሚቴ

1. የክልሉ ርዕሰ መስተዳደር – ሰብሳቢ
2. የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳደር – ም/ሰብሳቢ
3. የክልሉ የፀጥታ እና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ – አባል
4. የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽነር – አባል
5. የክልሉ ፍትህ ቢሮ/ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ – አባል

አዲስ አበባ 24/2/2014

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት በመላው ኢትዮጵያ ከጥቅምት 23/2014 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ እንደሚሆን የደነገገው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለስድስት ወራት የሚቆይ ነው።**

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን የሚከታተለውና የሚያስፈጽመው 'የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ' ሲሆን ዕዙ በአገሪቱ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም የሚመራ ሲሆን የተለያዩ አካላትን በማካተት ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል ተብሏል።

ይህ "በአገር ህልውና እና ሉዓላዊነት ላይ የተደቀነን አደጋ ለመከላከል የወጣ አዋጅ ቁጥር 5/2014" የተባለው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በውስጡ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያዎችን ይዟል።

አዋጁ እንዲከናወኑ የሚጠበቁ ተግባራት ምንድን ናቸው፣ ምን ግዴታዎችን ጥሏል፣ ምን ይከለክላል?. . .

**በአስቸኳይ ጊዜ የሚወሰዱ እርምጃዎች**

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ የአገርን ህልውና እና ሉዓላዊነት እንዲሁም የሰላማዊ ዜጎችን ደኅንነት ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን፡

1. በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል መከላከያ ኃይልን ወይም የትኛውንም ሌላ የፀጥታ አካል በማሰማራት ሰላምና ፀጥታ እንዲያስከብሩ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤
2. እድሜያቸው ለወታደራዊ አገልግሎት የደረሱ እና የጦር መሳርያ የታጠቁ ዜጎች ወታደራዊ ስልጠና እንዲወስዱ፣ ወታደራዊ ግዳጅ እንዲቀበሉ ወይም ይህን ማድረግ የማይችሉ ሲሆን በአማራጭ ትጥቃቸውን ለመንግሥት እንዲያስረክቡ ሊያዝ ይችላል፤
3. የሰዓት ዕላፊ ገደብ ሊወሰን ይችላል፤

4. ማናቸውም የሕዝብ የመገናኛ እና የሕዝብ መጓጓዣ ዘዴ እንዲዘጋ ወይም እንዲቋረጥ ሊያዝ ይችላል፤

5. ከሽብር ቡድኖች ጋር ይተባበራል ብሎ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የተጠረጠረ ማንኛውንም ሰው ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በቁጥጥር ሥር ለማድረግ፣ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ሆኖ ባለበት ጊዜ ድረስ ይዞ ለማቆየት ወይም በመደበኛ ሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ለማድረግ ይችላል፤

6. ከሽብር ቡድኖች ጋር ይተባበራል ብሎ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የተጠረጠረ ማንኛውንም ሰው ወይም ድርጅት ንብረት የሆነን ማንኛውንም ቤት፣ ህንጻ፣ ቦታ፣ መጓጓዣ ለመበርበርና እንዲሁም ማንኛውንም ሰው ለማስቆም፣ ማንነቱን ለመጠየቅ፣ ለመፈተሽ ይችላል፤ በብርበራ ወይም በፍተሻ የተያዙ የጦር መሳሪያዎችን መውረስ ይችላል፤

7. ለተወሰነ ጊዜ መንገዶችን፣ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ለመዝጋት እንዲሁም ሰዎች ለጊዜው በተወሰነ ቦታ እንዲቆዩ፣ ወደ ተወሰነ አካባቢ እንዳይገቡ ወይም ከተወሰነ ቦታ እንዲለቀቁ ለማዘዝ ይችላል፣

8. ከፍተኛ የፀጥት ችግር እና ስጋት በተፈጠረባቸው የአገሪቱ ክፍሎች የአካባቢ አመራር መዋቅርን በከፊልም ሆነ በሙሉ፣ ማገድ፣ መለወጥ እና በሲቪልም ሆነ በወታደራዊ አመራር መተካት ይችላል፤

9. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሽብር ቡድኖች የሞራልም ሆነ የቁስ ድጋፍ ያደርጋል ብሎ የሚጠረጥረውን የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት እንቅስቃሴ በሚመለከተው ባለሥልጣን በኩል እንዲታገድ ወይም ፍቃዱ እንዲሰረዝ ሊያዝ ይችላል፤

10. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሽብር ቡድኖች የሞራል ድጋፍ ያደርጋል ብሎ የሚያምነውን የመገናኛ ብዙኃንን ወይም ጋዜጠኛ በሚመለከተው ባለሥልጣን በኩል እንዲታገድ ወይም ፍቃዱ እንዲሰረዝ ሊያዝ ይችላል፤

**የተከለከሉ ተግባራት እና ግዴታዎች**

1. ሁሉም ሰው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ በአዋጁ መሰረት የሚያወጣቸውን መመሪያዎች እና የሚሰጣቸውን ትዕዛዞች የመቀበል ግዴታ አለበት።

2. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙን እንቅስቃሴ እና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን አላማ የሚቃረን፣ የሚቃወም እና ለሽብር ቡድኖች አላማ መሳካት አስተዋፅኦ የሚያደርግ፣ የሽብር ቡድኖችን የሚያበረታታ፣ ሰላማዊ ዜጎችን የሚያሸብር ንግግር በማንኛውም መንገድ ማድረግ ወይም ማሰራጭት የተከለከለ ነው።

3. በየትኛውም መንገድ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሽብር ቡድኖች የገንዘብ፣ የመረጃ፣ የቁስም ሆነ የሞራል ድጋፍ ማድረግ የተከለከለ ነው።

4. አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ በተዋረድ ውክልና ከሰጣቸው አካላት ፈቃድ ውጪ ማንኛውንም የአደባባይ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ የተከለከለ ነው።

5. ከመከላከያ፣ ከፌዴራል ፖሊስ ወይም ሌሎች ፈቃድ ከሚሰጣቸው የፀጥታ አካላት ወይም ከእነዚህ አካላት እውቅና እና ፈቃድ ውጭ ማናቸውንም የጦር መሳርያ ይዞ መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው።

6. በከተሞች አካባቢ የነዋሪ መታወቂያ የመንጃ ፈቃድ፣ የሠራተኛ መታወቂያ፣ ፓስርፖርት ወይም ከእነዚህ ተመጣጣኝ የሆነ መታወቂያ ሳይዙ መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው። [ዜጎች እነዚህን ሰነዶች የሚያገኙበት መንገድ ተመቻችቷል]

7. ማንኛውንም ወሳኝ በሆነ የአገልግሎት ዘርፍም ሆነ በምርት ሂደት ላይ የሥራ ማስተጓጎል ወይም የኢኮኖሚ አሻጥር መፈፀም የተከለከለ ነው።

8. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን አፈፃፀም ሰበብ በማድረግ የግል ጥቅም ለማግኘት ስልጣንን አላግባብ መጠቀም፣ ምክንያታዊ የሆነ ጥርጣሬ ሳይኖር ሆን ብሎ ዜጎችን ማሰር ወይም መሰል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው።

**ተፈፃሚነታቸው የታገዱ ሕጎች**

1. በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እሲኪጠናቀቅ ድረስ የትኛውም የዳኝነት አካል ስልጣን አይኖረውም።

2. በቪዬና ኮንቬንሽን የተመለከተው የዲፕሎማቲክ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ የፍሬ ነገርና የሥነ ሥርዓት ሕጎች ይህ አዋጅ በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ተፈፃሚነታቸው ታግዶ ይቆያል፡፡

**የወንጀል ተጠያቂነት**

1. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በአዋጁ መሰረት የወጡ መመሪያዎችን ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም እንደጥፋቱ ክብደት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

2. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በአዋጁ መሰረት የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ የተፈፀመው ወንጀል በሌሎች ሕጎች ከዚህ ከፍ ያለ ቅጣት የሚያስከትል ከሆነ የከበደው ቅጣት ተፈጻሚ ይሆናል።

3. በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ወቅት የተፈፀሙ የአዋጁ እና በአውጁ ማዕቀፍ የወጡ መመሪያዎች ጥሰቶች የአዋጁ ተፈጻሚነት ጊዜ ቢያበቃም፣ የሚያስከትሉት የወንጀል ተጠያቂነት በመደበኛው የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ መሰረት ይቀጥላል።